


# ETHIOPIAN FREE-PRESS JOURNALISTS IN EXILE

July 20, 2011

በኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ መብት እንዲከበር ከእስር ጀምሮ የህይወት መስዋዕትነት ተከፍሏል። ይህም የነጻነት ትግል ከትውልድ ወደ ትውልድ የወረደ፣ ለአመታት ያህል የዘለቀ ነው። ሆኖም አሁን በስልጣን ላይ ያለው አስተዳደር ይህንን በዜጎች መስዋዕትነት የቆየ ጭላንጭል ነጻነት መና ለማስቀረት ሰፊ የጥፋት ስራ በመስራት ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በዙፋናዊው፣ በወታደራዊ አስተዳደር አልያም አሁን በወያኔ አገዛዝ ስር ባለችበት ዘመን፤ ለፕሬስ ነጻነት እውን መሆን ሲሉ የታሰሩ፣ የተንገላቱ፣ የተሰደዱና የህይወት ዋጋ የከፈሉ ኢትዮጵያዊያን በሺዎች ይቆጠራሉ። የ'ነዚህ ታላላቅ ኢትዮጵያዊያን ህልምና ምኞት እንዲሳካ፤ በመቃብራቸውም ላይ የፕሬስ ነጻነት እንዲፈካ በምንሻበት በአሁኑ ዘመን... የጊዜው ባለስልጣናት ከቀድሞዎቹ ገዢዎች በባሰ መልኩ የቅጣት በትራቸውን አጠንክረውብናል። ሃሳብን በነጻነት ለመናገር እና ለመጻፍ የማይቻልባት አገር አያደረጓትም ነው - ኢትዮጵያን።

የይስሙላውን የ1985 ዓ.ም. የፕሬስ አዋጅ፤ በሌላ አዋጅ ቀይረው የነጻነትን ጭላንጭል ለማጥፋት ከመቼውም ጊዜ በላይ እየተንቀሳቀሱ ናቸው። ሊጠፋ የተቃረበውን የዲሞክራሲ ጭላንጭል በመጠቀም ሃሳባቸውን በጽሁፍ የሚገልጹ ጋዜጠኞችም... ሰብዓዊ መብታቸው ተነጥቆ፣ የእስር ሰንሰለታቸው ጠብቆ በእስር ቤት ውስጥ እየማቀቁ ይገኛሉ። ይህ አይነቱን የፍትህ መጓደል በመቃወም፤ ለህይወታቸውም በመስጋት ከመቶ በላይ ጋዜጠኞች ለስደት ሲዳረጉ፤ ሌሎች ደግሞ እራሳቸውን ከሙያው ለማግለል ተገደዋል።

በቅርቡ የታሰሩት ሁለት ጋዜጠኞች በፕሬስ አዋጁ ወይም በህገ መንግስቱ ወይም በወንጀለኛ መቅጫው ህግ መሰረት የሚያስቀጣቸው ወንጀል ባለመኖሩ፤ አዲስ የአሸባሪነት ህግ ተዘጋጅቶ... የፀደቀበት ፊርማ ሳይደርቅ ነው በአሸባሪነት ወንጀል የተከሰሱት። ትላንት ሃሳብን በነጻነት ሲገልጹ የነበሩ ነጻ ጋዜጠኞች የ"አሸባሪነት" ቅፅል ተሰጥቷቸው፤ እስከ አስራ አምስት አመት በሚያስፈርድ አዲስ አዋጅ ታስረው፤ የወጣትነት እድሜያቸውን በእስር ቤት እንዲያሳልፉ ተደርጓል።

የአውራምባ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ውብሸት ታዬ እና የፍትህ ጋዜጣ አምደኛ ርዕዮት አለሙ እንደወንጀል ተቆጥሮ ያሳሰራቸው አንድ እውነት ቢኖር፤ እውነትን ለህዝብ መናገራቸው ነው። ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ በትንታግ ብዕራቸው እውነትን መስክረው ይሆናል። ይህም እውነታቸው የገዢዎችን ጎራ አሸብሮት ሊሆን ይችላል። ሆኖም ለህዝብ እውነትን ስለተናገሩ በአሸባሪነት ተፈርጀው ለእስር መብቃታቸው ግን እያንዳንዱን ዜጋ ሊያስቆጨው ይገባል። ትላንት ለህዝቡ የቆሙ ጋዜጠኞች አሁን በእስር ላይ በመሆናቸው ለራሳቸው ሊቆሙ አልቻሉም፤ በመሆኑም ህዝቡ ለእነሱ የሚቆምበት ጊዜው አሁን ነው።

እያንዳንዱ የነጻ ፕሬስ ወዳጅ፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ይህንን ጉዳይ በቸልታ ሊያልፉት አይገባም። ለልዩ ልዩ የአገር ውስጥ እና የውጭ ድርጅቶች እውነታውን ለማሳወቅ በምናደርገው አዲስ ዘመቻ ውስጥ በመሳተፍ፤ ከኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ጎን እንዲቆሙ፤ ስለፕሬስ ነጻነት በተሰዉት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስም ኢትዮጵያዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

Kifle Mulat,
Ethiopian Free-press Journalists Association President.
Tel. 713 572 5484 (USA)
kiflem@sbcglobal.net / efjakifle@gmail. com

Dawit Kebede,
Chairman of Ethiopian Free-press Journalists in Exile
Please Do not hesitate to call me at 678 437 5597 (USA)
www.ethioforum.org
Email - media.emf@gmail.com